# በስልጣን ላይ ላሉት ቃሉን ጸልዩ

## Pray the Word for Those in Authority

in Amharic

**እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።**
1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:1-4

- ይህ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እንደምትጸልዩ፣ ወደማን እንደምትጸልዩ፣ ለምን እንደምንፀልይ እና ስለምን እንደምንፀልይ ይነግራችኋል።

- **እንዴት እንፀልይ፡ በልመና፣ በጸሎት፣ በምልጃ እና በምስጋና፤** የተለያዩ ዓይነት ጸሎቶችን ልትማሩ እና በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት ልትፈቅዱ ነው። እዚህ ጋር ልብ በሉ፡ ሁሉም ዓይነቶች ጸሎቶች ብዙ ቁጥር ናቸው፤ ይህ ብዙ ጸሎትን ያመለክታል።

- **ወደማን እንፀልይ ፡ ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ። ለምን እንፀልያለን፡** በጦርነት እና/ወይም በስቃይ ከመኖር ይልቅ እግዚአብሔርን በመከተል ሕይወትን በሚያከብር ማኅበረሰብ መካከል **ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፤**

- **ስለምን እንፀልይ፡ <<<ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ >>** 1ጢሞ.2፡4
  መዳን እድሜ ልክ ሥራ የሚጠይቅ ብዙ ነገርን ያቀፈ ቃለል ነው። (ፊል.2፡12)
  ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ የመቀብ የመ  መሪያው መረጃ እግዚአብሔርን ከማወቅ የሚያግደንን ኃጢአትን ያስወግድልናል። መንፈሳችን ዳግም የተወለደ ነው እና ለእግዚአብሔር እንደዚሁም ለመንፈሳዊ ነገሮች ሕያው ነን። (ዮሐ.3፡5-8)

  መዳን፡- ለመዳን የአዲስ ኪዳኑ የግሪክ ቃል ሶዞ ሲሆን ዳነ ማለት ነው። ሉቃስ 7 እና 8 የተለያዩ የመዳን ገፅታዎችን ያሳየናል፡ ከኃጢአት ይቅር መባል፣ አካላዊ ጥበቃ፣ ነፃ መውጣት፣ አካላዊ ፈውስ እና ተዓምራዊ ኃይልን ያካትታል።

- **ስለምን ከ1ጢሞ. 2፡4 የቀጠለ <<ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ >>**
  ዳግም በተወለደው መንፈሳችን ስለእግዚአብሔር የማዳን እና ከዓለም የሚለየውን የእግዚአብሔርን መንግስት ስለሚገዛው እውነቱ ልምምዳዊ እውቀት ሊኖረን ነው።
  ስለፀሎት መልስ ማረጋገጫ አለ፡

- **በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።** 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:3
  ይህ ጥቅስ በቁጥር 2 እና 4 ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጠቅሳል፡ ሁሉም ሰው እንዲድን፣ እውነትን እንዲያውቅ እና ጸጥ እንደዚሁም ዝግ ብሎ እግዚአብሔርን እንዲመስልና እና ጭምት እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ሁሉም ሰው እንዲድን፣ እውነትን እንዲያውቅ እና ጸጥ እንደዚሁም ዝግ ብሎ እግዚአብሔርን እንዲመስልና እና ጭምት እንዲሆን በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነው። በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነው ማለት ከእርሱ ስለሚመጣ ጸሎቱ መልካም ፣ እግዚአብሔራዊ እና በእርሱ ፊት ተቀባይነት ያለው ነው። ስለዚህ ይመልሳል። እነዚህ ጸሎቶች በእግዚአብሔራዊነት እና በፍር  ት ጸጥ እና ዝግ ሕይወት በመስጠት ይጠቅሙናል።